# የምርጫ አስፈፃሚዎችና የህዝብ ታዛቢዎች የገለልተኝነት ጥያቄ!

**ከብድሆ**

bidiho@yahoo.com

ማንም ሰው ወደዚህች ዓለም ከተቀላቀለበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ሁኔታዎች ማለፉ አይቀሬ ነው። ይህቺ ዓለም ለአንዱ ጥሩ ለሌላው ደግሞ በተቃራኒው ስጦታዋ እየሰጠች፣ ያው የተለመደው ዑደቷን ትቀጥላለች። ሰው በዚህ ውጣ ውረድ ውስጥ በተፈጥሮ የሚቸረው ጥሩ/መጥፎ ባህርይ እንዳለ ሆኖ፣ በአካባቢ ተፅዕኖ ምክንያት የሚወርሰውን ባህርይ ይኖረዋል። እነዚህን ባህርያቶች የስነልቦና ባለሙያዎች Nurture and Nature ይሏቸዋል። ከነዚህ በተፈጥሮና በአካባቢ ተጽዕኖ የሚገኙ ሁለቱ ባህሪያቶች፣ በሰው ባህሪ ላይ ከሚያደርሱት ተፅዕኖ አንጻር ሲታይ የአንበሳው ድርሻ የሚይዘው የአከባቢ ተፅዕኖ /Nurture/ ነው።

በመሆኑም "ሰዎች አከባቢያቸውን ይመስላሉ"፣ "ማን እንደሆንህ ለማወቅ ከማን ጋር እንደምትሄድ ንገረኝ" የሚሉ የአገሬ ሰው አባባል፣ አካባቢ በሰው ላይ ከሚያደርሰው ተፅዕኖ በመነሳት ይሆናል የሚል ግምት አለኝ። በመሆኑም ማንኛውም ሰው በዓለም ከሚከናወኑ የተለያዩ ክስተቶች የአንዱን ተጽዕኖ ሳያርፍበት ሊኖር ይችላል የሚል አስተሳሰብ አይኖርም።

ማንኛውም ሰው ከአከባቢ ተፅዕኖ ሊያመልጥ አይችልም ሲባል ማንም ሰው ገለልተኛ ሊሆን አይችልም ማለት እንዳልሆነ ግን ፀሐይ የሞቀው ሐቅ ይመስለኛል። እንዲህ ቢሆን ኖሮማ በዴሞክራሲ የዳበሩ አገራት ገለልተኛና ነፃ ፍርድ ቤት፣ ገለልተኛ ፖሊስ፣ በአጠቃላይ ገለልተኛ ተቋም የሚባል ነገር አይኖርም ነበር።

ገለልተኝነት /Imprtiality/ ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለሱ ተገቢ ይመስለኛል። በኢንሳይክሎፔድያ መፅሐፍ ስለ ገለልተኝነት ሲናገር «Impartial means not biased, having no direct involvement or interest and not favoring one person/group/peer/party or side more than another with the existing law» ብሎ ይገልፀዋል። ይህንን አገላለፅ አንድ ሰው/ተቋም ገለልተኛ የሚባለው ለአንዱ ወግኖ ለሌላ

የሚያደላ ካልሆነና ለሁሉም ባለው ሕግ መሰረት በእኩልነት የሚያገለግል/የሚያስተናግድ እንደሆነ ነው የሚያስገነዝበን።

ሰሞኑን በተለያዩ የግል ሕትመቶች የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም፣ የህዝብ ታዛቢዎቹ ገለልተኛ አይደሉም፣ የምርጫ አስፈፃሚዎቹ ገለልተኛ አይደሉም የሚሉ ወሬዎች በተለያዩ ሕትመቶች አንብቤያለሁ። እነዚህ በሙሉ ገለልተኛ ስላልሆኑ መጪውን ምርጫ ነፃ፣ ፍትሃዊ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ብሎም በህዝብና በፖለቲካ ድርጅቶች ዘንድ ተአማኒ ለማድረግ አይቻልም በማለት አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች ሲደመድሙ አስተውያለሁ። እኔም እንደ ዜጋ ይህን የምርጫ አጀንዳ ትልቅ ትኩረት ሰጥቼ እየተከታተልኩት ስለነበርና አሁንም እየተከታተልኩ ስለሆነ፣ እኔ ብቻ ሳልሆን መላ ህዝቡ የሉዓላዊነቱ መገለጫ የሆነውን ምርጫ እየተከታተለ ስለሆነ፣ ያለኝን አስተያየት ማቅረብ ወደድኩ።

በመጀመርያ የምርጫ ቦርድ አባላት በምን ሁኔታ እንደተመረጡ አብዛኛዎቻችን እናውቀዋለን። እንደሚታወቀው የቦርዱን አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሚሾሙ ሕገመንግስቱ ይደነግጋል። በተሻሻለው የምርጫ ሕግ አንቀፅ 6/2 «ጠቅላይ ሚኒስትሩ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰዎችን ለቦርድ አባልነት ለምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት፣ በምክር ቤቱ መቀመጫ ያላቸው ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች፣ እጩ ሊሆኑ የሚችሉ ግለሰቦች ነፃና ገለልተኛ መሆናቸውን በማረጋገጥ ጉዳይ ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችል በቂ የምክክር መድረክ እንዲኖር ያደርጋል» ይላል። በዚህ መሰረት፣ በምክርቤት መቀመጫ ያላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገለልተኛ ያሏቸውን ሰዎች በመጠቆም፣ የቦርዱ አባላት እንዲሆኑ የተደረገበት ሁኔታ እንዳለ በተደጋጋሚ በመገናኛ ብዙሃን ሰምተነዋል። ይህን በሰማሁ ጊዜ መጪውን ምርጫ ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ነፃና ፍትሃዊ እንደሚሆን ገምቻለሁ።

የምርጫ ቦርዱ አባላት ገለልተኝነት በአመራረጡ ሂደት ብቻ ሳይሆን በተግባር አሳይተዋል ወይስ አላሳዩም? የሚል ጥያቄ መጠየቅ ተገቢ ይመስለኛል። እኔ ከማስታውሳቸው ተግባራት በመጀመርያ 16 የሚሆኑ የቦርዱ መመሪያና ደንብ ሲወጡ ከሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመመካከርና በመወያየት ብሎም በመስማማት ነው። አንድም መመሪያ ወይም ደንብ፣ ያለ ፓርቲዎቹ ምክክርና ውይይት የወጣ የለም። ይሄ የሚያሳየው ቦርዱ ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በእኩልነት እያገለገለ መሆኑ ነው።

በሌላም፣ ቦርዱ በአገራችን ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዘርፈ ብዙ ነገሮች ሊጠናከሩ እንደሚገባ ተገንዝቦ የፋይናንስ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸውና፣ ለዚህ ማስፈፀሚያ የሚሆን ቀመር ከፖለቲካ ፓርቲዎቹ ጋር በመስማማት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ ብዛት 55%፣ ዕጩ ተወዳዳሪ ብዛት 25%፣ ለሴት ዕጩዎች ብዛት 10% እንዲሁም ለሁሉም ፓርቲዎች እኩል የሚከፋፈል 10% ቀመር አዘጋጅቶ ፓርቲዎቹ ተስማምተው ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። እኔ እንደማውቀው ከሆነ አብዛኞቹ አገሮች ለፖለቲካ ፓርቲዎች የፋይናንስ ድጋፍ ሲያደርጉ እስከ 90% የሚሆነውን በምክርቤቱ ባለው መቀመጫ ነው የሚሰጠው። ይሁን እንጂ ምርጫ ቦርዱ በአገራችን ያሉት ተቃዋሚዎች መጠንከር ይገባቸዋል ብሎ በአባትነት መንፈስ እንዲህ ጥሩ ተግባር እየሰራ ሳይ በትክክል ቦርዱ ገለልተኛ እንደሆነ ተገንዝቢያለሁ።

የምርጫ ቦርዱ አባላት ገለልተኛ ከሆኑ ከስራቸው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚዎችም ገለልተኛ ሊሆኑ እንደሚገባ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም። ምክንያቱም እነዚህ የምርጫ አስፈፃሚዎች የምርጫ ቦርዱ ራእይና ዓላማ ሊያሳኩ የሚመረጡ ናቸው። ቦርዱ በምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ ያደረገው ነገር ካለ፣ የተለያዩ ቡድኖች ከማዕከሉ ልኮ፣ ገምግሞና ገለልተኛነታቸው አጣርቶ ከ60-70% የሚሆኑ የምርጫ አስፈፃሚዎች በአዲስ እንዲተኩ አድርገዋል። እንደሚታወቀው በአገራችን 220 ሺ የሚሆኑ የምርጫ አስፈፃሚዎች አሉ። ከነዚህ ከ 60-70%ቱ ጊዜ ተወስዶ ብዙ ወጪ ወጥቶበት ሊቀየሩ የተደረገበት ዋና ምክንያት፣ የምርጫ ቦርዱ ራእይን በሚገባ ሊያስፈፅሙ የሚችሉ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው። ቦርዱ ያደረገው ይሄ ብቻ አይደለም ነባሮቹና አዲሶቹ የምርጫ ክልል ሃላፊዎች በቂ የሆነ የዓቅም ግንባታ ስልጠና ሰጥቶ እነሱም በየደረጃው ላሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች እንዲያሰለጥኑ ተደርገዋል። ሁሉም ያላቸውን ሃላፊነት በሚገባ እንዲገነዘቡ ሆነዋል።

ይሁን እንጂ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የምርጫ አስፈፃሚዎቹ ገለልተኛ አይደሉም፣ የኢህአዴግ ካድሬዎች ናቸው፣ ብለው አስተያየት ሲሰጡ ይስተዋላሉ። የምርጫ ቦርድ አባላት መግለጫ ሲሰጡ ደግሞ «የሚባለውን ወሬ በተጨባጭ ካለ ከነማስረጃው ከቀረበልን ያለአንዳች መወላወል እናባርረዋለን። የፓርቲ አባል የሆነ የምርጫ አስፈፃሚ ለቦርዱ አይጠቅምም ለህዝቡም አይጠቅምም።» ሲሉ ይደመጣሉ። እኔም የምጋራው ነገር ካለ ይሄ የምርጫ ቦርድ ንግግር ነው። ምክንያቱም ቦርዱ ከአመላመሉና ከሚያደርገው ያለ እንቅስቃሴ አንፃር የፓርቲ አባል የሆነ የምርጫ አስፈፃሚ ይመለምላል የሚል እምነት

ስለሌለኝ ። የፖለቲካ ፓርቲዎችም በጅምላ ስም ከማጥቆር ተቆጥበው በማስረጃ የተደገፈ ክስ ቢያቀርቡ መልካም ነው እላለሁ።

በሌላ ግርምት የፈጠረልኝ ነገር ቢኖር፣ የህዝብ ታዛቢዎች ገለልተኛ አይደሉም የሚል የተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ንግግር ነው። እነዚህ የህዝብ ታዛቢዎች የሚመረጡ በህዝብ ነው። የህዝብ ታዛቢዎች ከሌሎች ታዛቢዎች በላይ ሃላፊነትና እምነት የሚሰጣቸው የህዝቡ ጆሮና ዓይን ሆነው ሊያገለግሉ በሕዝብ የተመረጡ በመሆናቸው ነው። እነዚህ ታዛቢዎች የህዝቡ የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤትነት በሚገባ እንዲያረጋግጡለት፣ ህዝቡ የመረጣቸው ናቸው። ከመመረጣቸው በፊት በምርጫ ቦርድ ለህዝቡ ለፖለቲካ ፓርቲዎች በተለያዩ የህዝብ ሚድያዎች ጥሪ ተላልፎ እንደነበር አስታውሳለሁ። ከዛ በኋላ የህዝብ ታዛቢ ምርጫ ተካሂዶ ነበር። ይሁን እንጂ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው የኛ ወኪሎች አልነበሩም፣ ጥቂት ህዝብ ብቻ ወጥቶ ነው የመረጠው፣ በህዝብ ታዛቢነት የተመረጡ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች ናቸው በመሆኑም የህዝብ ታዛቢ ምርጫ ይደገምልን፣ ብለው ለምርጫ ቦርድ ክስ ማቅረባቸው አስታውሳለሁ። ምርጫ ቦርድም ይሄንን ክስ በሚገባ መርምሮ በቂ ህዝብና የተቃዋሚ ፓርቲዎች ወኪል ያልነበረበት ቦታ እንደገና ምርጫ እንዲካሄድ መወሰኑ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። በአዲስ አበባ ከ89 ቀበሌዎች በ59ኙ ቀበሌዎችና ጥቂት ችግር የነበረባቸው ክልሎች የህዝብ ታዛቢዎች ምርጫ እንደገና እንዲካሄድ ተደርገዋል።

ምርጫ ቦርዱ የተፈጠረውን ስህተት አይቶ በአስቸኳይ እርምት እንዲወሰድ ማድረጉ፣ ሁሉም ፓርቲዎች በገለልተኝነትና በእኩልነት እያገለገለ ያለ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ በየቀበሌው የሚፈለገው ህዝብና የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በተገኙበት የተመረጡ የህዝብ ታዛቢዎች ገለልተኛ አይደሉም ብሎ መናገር ጊዜው ሰውቶ ይወኩሉኛል ብሎ የመረጠ ህዝብን እንደመሳለቅ ሆኖ ነው የሚሰማኝ። ይህ ደግሞ ትክክልም ተገቢም አይደለም፣ ሊታረም ይገባል።

ምርጫ ቦርድ የሚሰራቸው ያሉ አበረታታች ስራዎች ልናደንቅለትና ልናበረታታው ይገባል እንጂ በተጨባጭ ባልተደገፉ የመንደር ወሬዎች ስራውን በዜሮ ማባዛት የለብንም። ይሄ ማለት በአፈፃፀም ላይ የሚከሰቱ ችግሮች የሉም እያልኩ እንዳልሆነ ልትገነዘቡልኝ እወዳለሁ። በሂደቱ እንዳየነው የተፈጠሩት ችግሮች በአስቸኳይ

እያረመ የሚሄድ ያለ ቦርድ ነው። ቦርዱ ካሁን በኋላ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችም በአስቸኳይ ማረም እንደሚገባው በዚህ አጋጣሚ ልገልፅለት እፈልጋለሁ።

በመጨረሻ መጪው ምርጫ ነፃ፣ ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ ዴሞክራሲያዊና በህዝባችን ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተአማኒ የሚሆነው ሁሉም ባለድርሻ አካላት ባለው ሕግ መሰረት በቁርጠኝነት ሲሰሩ ነው። ይሁን እንጂ ፓርቲዎቻችን በተጨባጭ የሚታዩ የቦርዱ ስራዎች ጥላሸት የሚቀቡት ከሆነ በአገራችን እያበበ ያለውን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የሚያኮላሽ በመሆኑ ይህንንም ለፓርቲዎቹም ለህዝባችንም እንደማይጠቅም ከዚህ በፊት ተምረናልና፣ በምክንያዊነትና ባለው ሕግ (Existing Law) ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ጨዋታ ቢካሄድ የተሻለ ነው እላለሁ።

ሰላም!